# የመዋለ ሕጻናት የክፍያ መጠንና የገንዘብ እርዳታ

**በእኔ አካባቢ ያለው የመዋለ ሕጻናት ወጪ ምን ያህል ነው?**

በሚኖሩበት አካባቢ የመዋለ ሕጻናት አማካይ ወጪ ስንት እንደሆነ ለማወቅ ይህንን ሰንጠረዥ ይጠቀሙ። የተዘረዘረው የክፍያ መጠን ለአንድ ሳምንት የሙሉ ቀን እንክብባቤ አማካይ ወጪው ነው። ይሁን እንጂ ሰፋ ያሉ የተለያዩ የክፍያ መጠኖች እንደሚኖሩ ሊጠብቁ ይገባል።

- በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት መስጪያዎች

**ለመዋለ ሕጻናት ለመክፈል እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?**

- ከሲያትል ከተማ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?
- ከኪንግ ካውንቲ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?
- መኖሪያ ቤት የለሽ ከሆንኩስ?
- ከዲኤስኤችኤስ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?
- በሬድመንድ ከተማ ውስጥ የምኖር ከሆነስ?
  - የሬድመንድ ከተማ ስኮላርሽፕ መመሪያዎች (አክሮባት)
  - የሬድመንድ ከተማ ስኮላርሽፕ ማመልከቻ (አክሮባት)

የሲያትል ከተማ ፡ ኪንግ ካውንቲ፣ የሬድመንድ ከተማ፣ እና ዲኤስኤችኤስ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለመዋለ ሕጻናት እንዲከፍሉ ይረዷቸዋል። እርዳታ ለማግኘት ሥራ መሥራት ወይም በተፈቀደ የስልጠና ፕሮግራም ውስጥ መሆንና የገቢ መመሪያ ነጥቦችን ማሟላት ያስፈልገዎታል። ቋሚ መኖሪያ የሌላቸው ቤተሰቦች ከኪንግ ካውንቲ ለሚገኘው ልዩ እርዳታ ብቁ ናቸው።

**ከሲያትል ከተማ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?**

ከዚህ ፕሮግራም እርዳታ ለማግኘት በሲያትል ከተማ ክልል ውስጥ መኖርና ሌሎቹን አስፈላጊ ነጥቦችን ማሟላት አለብዎት። ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው ከአንድ ወር እስከ 12 ዓመት ለሆናቸው ልጆች አገልግሎት ይሰጣል። ቤተሰቦች በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከ160 በላይ ከሆኑት ከሲያትል ከተማ ጋር ኮንትራት ካላቸው የመዋለ ሕጻናት ቤቶችና ማዕከላት ውስጥ ይመርጣሉ። ለዚህ ፕሮግራም ተራ መጠበቅ ሊኖር ይችላል።

ማመልከቻ ለማስገባት፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች ጊዜ (206) 386-1050 ይደውሉ።
ዌብ ሳይት፣ http://www.cityofseattle.net/hsd/ChildCareSubsidies/Default.htm

**ከኪንግ ካውንቲ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?**

ከኪንግ ካውንቲ ፕሮግራም እርዳታ ለማግኘት በኪንግ ካውንቲ ውስጥ መኖርና ከሲያትል ከተማ ክልል ውጭ መኖር ያስፈልግዎታል። ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው ከአንድ ወር እስከ 12 ዓመት ለሆናቸው ልጆች አገልግሎት ይሰጣል። ለእርዳታ ብቁ የሚሆኑ ቤተሰቦች በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከሚገኙ ከተፈቀደላቸው የመዋለ ሕጻናት ቤቶችና ማዕከላት ውስጥ መምረጥ ይችላሉ። ለዚህ ፕሮግራም ተራ መጠበቅ ሊኖር ይችላል። <u>ማሳሰቢያ፣ በታቀደው የባጀት መቀነስ ምክንያት ኪንግ ካውንቲ ባሁኑ ጊዜ አዲስ ማመልከቻ አይቀበልም። የከተማ ክልል ባልሆነ ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች (በማንኛውም የከተማ ክልል ውስጥ የማይኖሩ) ለ 2002 ጥቂት ባጀት ሊኖር ይችላል</u>።

- ማመልከቻ ለማስገባት፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች ላይ (206) 296-1362 ይደውሉ፣ ወይም
- ዌብ ሳይት፣ http://www.metrokc.gov/dchs/csd/ChildCare/Subsidy.htm

**መኖሪያ ቤት የለሽ ከሆንኩስ?**

ዕድሜያቸው ከአንድ ወር እስከ 12 ዓመት የሆነ ልጆች ያላቸውን ወላጆች እርዳታ ለማቀረብ ኪንግ ካውንቲ ከመኖሪያ ቤት-የለሽ አገልግሎት መስጪያ መዋቀር ጋር ትብብር ያደርጋል።

ብቁ ለመሆን ቤተሰቦች ቋሚ፣ መደበኛ የምሽት ጊዜ መኖሪያ የሌላቸው መሆን ወይም በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ የሚኖሩ መሆን አለባቸው። ይህ የበጎ አድራጎት ሆቴልን፣ ከቤተሰብ ብጥብጥ የመገለያ መጠለያን፣ የመሰብሰቢያ መጠለያን፣ ወይም የመሸጋገሪያ ጊዜ መኖሪያን ሊያጠቃልል ይችላል።

- ማመልከቻ ለማስገባት፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች ላይ (206) 296-1362 ይደውሉ፣ ወይም
- ዌብ ሳይት፣ http://www.metrokc.gov/dchs/csd/ChildCare/Subsidy.htm

**ከዲኤስኤችኤስ እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?**

ከዲኤስኤችኤስ እርዳታ ለመቀበል የገቢ መመሪያ ነጥቦችን ማሟላትና ለተወሰኑ ጥቂት ሰዓቶች ሥራ መሥራት አለብዎት። በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ብዙ ጽ/ቤቶች አሉ። ለእርዳታ ብቁ ይሆኑ እንደሆነ ለማወቅ ወይም በአቀራቢያዎ የሚገኝ ጽ/ቤትን ስልክ ቁጥር ለማግኘት 1-877-980-9131 ይደውሉ። ማመልከቻውን በኦንላየን ማስገባት ይችላሉ። http://www.wa.gov/workfirst/workingfamilies

## በሬድመንድ የከተማ ክልል ውስጥ ከኖርኩስ?

የሬድመንድ ከተማ በመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ምንጭ በኩል የገቢ መመሪያ ነጥቦችን ለሚያሟሉና በሬድመንድ ከተማ ክልል ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች እስኮላርሽፕ ይሰጣል። ለዚህ ስኮላርሽፕ መምሪያ ነጥቦቹን ያሟሉ እንደሆኑ ለማወቅ እባክዎን 206-329-1011 የውስጥ ቁጥር 215 ይደውሉ።

- የሬድመንድ ከተማ ስኮላርሽፕ መመሪያዎች (አክሮባት)
- የሬድመንድ ከተማ ስኮላርሽፕ ማመልከቻ (አክሮባት)

## ተጨማሪ መረጃና ማገናኛዎች

- የገንዘብ እርዳታዎች